
# ድጎማዎትን በአስተማማኝ፥ በተመቻቸ እና በቀላል መንገድ ለመጠቀም ወደሚያስችልዎት **የዋሽንግተን ኤሌክትሮኒካዊ የድጎማ ማስተላለፊያ ዘዴ (EBT) እና የዋሽንግተን የQuest EBT ካርድ- እንኳን በደህና መጡ።**

መሰረታዊ የምግብ ድጎማ ለመጠቀም ብቁ ከሆኑ፥ የዋሽንግተን የ Quest EBT ካርድዎትን በመጠቀም ኦንላይን መግዛትን የሚያስችሉትን ጨምሮ ወደ ማንኛውም የዚህ መርሃ ግብር ተሳታፊ ወደሆነ ሱቅ ጎራ በማለት የተመረጡ ምግቦችን መግዛት ይችላሉ።

ድጎማዎትን በጥሬ ገንዘብ ለመውሰድ ብቁ ከሆኑ፥ የዋሽንግተን የQuest EBT ካርድዎትን በመጠቀም ገንዘብዎትን መውሰድ ይችላሉ፤ ወይም የዚህ መርሃ ግብር ተሳታፊ ወደ ሆነ ሱቅ ጎራ በማለት ሊገዙ እና ድጎማዎትን ወደሚያገኙዋቸው የ ATM ማሽኖች በመሄድ ሊወስዱ ይችላሉ።

## በጣም ቀላል ነው!



### የዋሽንግተን የ QUEST EBT ካርድዎትንሱቅ ውስጥ እንዴት እንደሚጠቀሙበት

1. ማንኛውንም ነገር ለመግዛት ከመሄድዎ በፊት ያለዎትን ቀሪ ሒሳብ www.ebtedge.com በመጎብኘት ወይ ወደ ደንበኞች ኣገልግሎት በመደወል ይወቁ።
2. የዋሽንግተን የQuest EBT ካርድዎትን ሽያጭ በሚከናወንበት ቦታ ፖይንት ሴል (POS) ላይ ማስገባት ወይም ካርድዎትን ለገንዘብ ተቀባይ ሰራተኛው መስጠት ይችላሉ።
3. ለገንዘብ ተቀባዩ ምን እንደሚፈልጉ ይንገሩት (ምግብ ወይስ ጥሬ ገንዘብ)።
4. ባለአራት አሃዙ የግል መለያ ቁጥርዎትን (PIN) በኪፓዱ ላይ ያስገቡ። ቁጥርዎትን ሲያስገቡ **** ይታያል።
5. OK ወይም ENTER የሚለውን ቁልፍ ይጫኑ።
6. ገንዘብ ተቀባዩ የገዙትን የገንዘብ መጠን በማስገባት ሲያሳይዎት ልክ ከሆነ YES የሚለውን ቁልፍ ይጫኑ።
7. ገንዘብ ተቀባዩ ደረሰኝ ይሰጥዎታል። በደረሰኙ ላይ ያለው መረጃ ትክክል መሆኑን ያረጋግጡ።
8. በሚቀጥለው ጊዜ የሆነ ነገር መግዛት ሲፈልጉ ያለዎትን ቀሪ ሒሳብ ማወቅ እንዲችሉ፥ የተቀበሉትን ደረሰኝ አይጣሉት።

ከላይ የተጠቀሱት ሒደቶች እንደሚያጋጥምዎት የPOS ማሽን ዓይነት ይለያያል። እገዛ ከፈለጉ ገንዘብ ተቀባዩን ይጠይቁት።

ከምግብ ድጎማ ተቀማጭ ሒሳብዎ ላይ የሚቀነሰው፥ ትክክለኛው የገዙትን የምግብ ዋጋ ብቻ ነው። የምግብ ድጎማ ግዢ ሲፈፅሙ፥ ሱቆች መልስ አይሰጡዎትም።

የገንዘብ ድጎማዎትን ወደ ሱቆች በመሄድ ገንዘብ ብቻ ለማውጣት መጠቀም ይችላሉ፤ ወይም ምግብም ምግብ ያልሆኑ ነገሮችም ለመግዛት ሊጠቀሙበት ይችላሉ (ሳሙና፥ ዳይፐር፥ ወዘተ)። ከጥሬ ገንዘብ ተቀማጭ ሒሳብዎ ከሆነ የሚገዙት፥ ሱቆቹ የገንዘብ መልስ ሊሰጡዎት ይችላሉ። ማንኛውንም ጥያቄ ካለዎት፥ ገንዘብ ተቀባዩን ይጠይቁት።




### የዋሽንግተን የ QUEST EBT ካርድዎትን በአውቶሜትድ መስጫ ማሽን (ATM) ላይ እንዴት ይጠቀሙበታል

(የጥሬ ገንዘብ ድጎማ ለማውጣት ብቻ የሚያገለግል፥ የምግብ ድጎማ በኤ.ቲ.ኤም. ማሽን ተጠቅሞ ማግኘት አይቻልም)

1. ካርድዎትን ያስገቡ።
2. የግል መለያ ቁጥርዎትን (PIN) ያስገቡና OK ወይም ENTER የሚለውን ቁልፍ ይጫኑ።
3. WITHDRAW CASH የሚለውን ቁልፍ ይምረጡ፥ ከዛም CHECKING የሚለውን ይምረጡ።
4. ማውጣት የሚፈልጉትን የዶላር መጠን ያለሳንቲም ያስገቡ ለምሳሌ $20, $40, $60 ወዘተ።
5. ተጨማሪ ክፍያ ከተጠየቁ፥
   - YES የሚለውን በመጫን አገልግሎቱን መጠቀምዎን ይቀጥሉ።
   - ተጨማሪውን ክፍያ መክፈል የማይገልጉ ከሆነ NO የሚለውን በመጫን አገልግሎቱን ያስቁሙት።
6. ካርድዎትን፥ ደረሰኝዎን እና ገንዘብዎትን ይውሰዱ። ኤ.ቲ.ኤም ማሽኑ ካርድዎትን ካልመለሰልዎት፥ ወደ 888-328-9271 በመደወል የደንበኛ አገልግሎት ያግኙ።
7. ገንዘብዎትን በመቁጠር ከደረሰኙ ጋር እኩል መሆኑን ያረጋግጡ።
8. የ ATMs ደረሰኙ መጠቀም የሚችሉትን ቀሪ ገንዘብ ያሳያል፡፡

ኤ.ቲ.ኤም. ማሽኑ በአንድ ጊዜ ማውጣት የሚችለው የገንዘብ መጠን ውስን ከሆነ፥ የገንዘብ ድጎማዎትን በሙሉ ማውጣት በሚፈልጉበት ወቅት በትንንሹ በማድረግ ማውጣት ሊኖርብዎት ይችላል። ገንዘቡን ከ ATM የሚያወጡ ከሆነ፥ በእያንዳንዱ ጊዜ ተጨማሪ ክፍያ ሊከፍሉ ይችላሉ።

## ከዋሽንግተን QUEST EBT ካርድ ጋር በተያያዘ የሚነሱ ጥያቄዎችና መልሶቻቸው

### የዋሽንግተን የ Quest EBT ካርድ በመጠቀም ጥቅም ማግኘት የምችለውን እንዴት ነው?

ተቀማጭ ሒሳብዎ ላይ በየወሩ ጥቅሞችን ወድያውኑ ይጨመርልዎታል። የወሩ ድጎማዎትን ማግኘት ከፈለጉ የዋሽንግተን የQuest EBT ካርድዎትን ይጠቀማሉ። ጥሬ ገንዘብ ለማግኘት ወይም ዕቃዎችን ለመግዛት ድጎማዎትን ከተጠቀሙ፥ ቀሪ ተቀማጭ ሒሳብዎ ይቀንሳል። ካርድዎት ካልጠፋ፤ ካልተሰረቀ ወይም ካልተበላሸ በስተቀር መቀየር አያስፈልግም፡፡

### ድጎማየን የማገኘው መቼ ነው?

ድጎማዎት የEBT ተቀማጭ ሒሳብዎ ላይ በወሩ በተመሳሳይ ቀን ይገባልዎታል። ይህም የሚሆነው የተመደበው ቀን በቅዳሜና እሁድ ወይም በበዓል ቀን ላይ ቢውልም ማለት ነው። ሁሉም ድጎማዎች ከጠዋቱ 9 ኤም ጀምሮ መውሰድ ይቻላል። በወሩ መጨረሻ ላይ የቀረ ገንዘብ ወደቀጣዩ ወር ይተላለፋል።

### የዋሽንግተን የ Quest EBT ካርዴን መጥቀም የምችለው የት ነው?

የዋሽንግተን የQuest EBT ካርድዎትን በመርሃ ግብሩ በሚሳተፉ በሀገሩ በሙሉ በሚገኙ ሱቆች እና ATM ማሽኖች (ለጥሬ ገንዘብ ጥቅም ብቻ) ላይ መጠቀም ይችላሉ። Quest የሚለውን ሎጎ ወይም ምልክት ባዩበት ቦታ ላይም ካርድዎትን መጠቀም ይችላሉ። Quest የሚለውን ሎጎ ወይም ምልክት ካላዩ፥ ካርዱን በመጠቀም ምግብ መግዛት ወይም ጥሬ ገንዘብ ማውጣት ይችሉ እንደሆነ የሱቁ ስራ አስኪያጅ መጠየቅ ይችላሉ።

### ካርዴ ከጠፋብኝ ምን ማድረግ አለብኝ?

የዋሽንግተን የQuest EBT ካርድዎት ከጠፋ፥ ከተሰረቀ ወይም ከተበላሸ ወደ ደንበኛ አገልግሎት ማዕከል 888-328-9271 ይደውሉ እና አገልግሎት እንዳይሰጥ ያስቁሙት፤ እንዲሁም ተለዋጭ ካርድ ይላክልዎታል፡፡

### የካርዴ ቁጥር ምንድን ነው?

የካርድዎ ቁጥር በካርዱ ፊት ለፊት ላይ የሚገኝ ባለ 16 አሃዝ ቁጥር ነው።

### ካርዴ ካልሰራስ?

ወደ ደንበኛ አገልግሎት ማዕከሉ ይደውሉና እገዛ ይደረግልዎታል። የዚህ ማዕከል ስልክ ቁጥር በካርዱ ጀርባ ላይ ይገኛል። የደንበኛ አገልግሎት ማዕከሉ ለ24 ሰዓትና በሳምንት ለሰባት ቀናት ክፍት ነው።

### በተቀማጭ ሒሳቤ ላይ የተሳሳተ ነገር ቢኖር ምን ማድረግ አለብኝ?

አንድ ባለ ሱቅ በኮምፕዩተር ችግር ምክንያት ከእርስዎ የዋሽንግተን የEBT መጠየቂያ ካርድ ከተገቢው በላይ ወይም ከሚገባው በታች ገንዘብ ከተከፈለው፥ በቀሪው ሒሳብዎ ላይ ማስተካከያ ይደረጋል። ይህ ማስተካከያ ባሁኑ ባለው ተቀማጭ ሒሳብዎ ወይም በሚቀጥለው ወር ሒሳብዎ ላይ ለውጥ ሊያመጣ ይችላል። ሒሳብዎን የሚቀንሰው ከሆነ፥ የዋሽንግተን የEBT መጠየቂያ ካርድ የማስተካከያ ማስታወቂያ በደብዳቤ ይላክልዎታል።

### ካርዴን በሚገባ መጠቀም የምችለው እንዴት ነው?

1. በካርድዎ ጀርባ ላይ ይፈርሙበት።
2. የግል መለያ ቁጥርዎትን (PIN) በካርድዎ ላይ አይፃፉት።
3. ካርድዎትን በጥንቃቄና በንፅህና ይያዙት።
4. ካርዱን አይጠፉት፡፡
5. ካርድዎትን ማግኔትና እንደ ቲቪ፥ ማይክሮዌቭ ወዘተ ከመሳሰሉት የኤለክትሮኒክ ዕቃዎች ባሉበት አከባቢ አያስቀምጡት።
6. ይህም የመኪና ዳሽቦርድ የመሳሰሉ ቀጥታ የፀሐይ ጨረር ባለበት ቦታ አያስቀምጡት።
7. ካርድዎትን አይጣሉት፥ ድጎማ በሚቀበሉበት በማንኛውም ወር የሚጠቀሙት በሱ ካርድ ነው
8. በተደጋጋሚ ካርድ መቀያየር በማጭበርበር ምርመራ ሊያስከትል ይችላል፡፡

### የግል መለያ ቁጥር (PIN) ምንድን ነው?

የግል መለያ ቁጥር (PIN) እርስዎ ብቻ በዋሽንግተን የQuest EBT ካርድዎትን እንዲጠቀሙበት የሚሰጥዎት ባለአራት አሃዝ የምስጢር ቁጥር ነው። የ EBT ካርድ ያለየግል መለያ ቁጥር (PIN) አይሰራም፡፡ ለማንኛውም ሰው የግል መለያ ቁጥርዎን አይንገሩ! ሌላ ሰው የግል መለያ ቁጥርዎትን ካወቀው፥ ካርድዎትን ተጠቅሞ የሚያገኙትን ድጎማ በሙሉ ሊወስደው ይችላል። ድጎማው ደግሞ የሚተካ አይደለም።

### የግል መለያ ቁጥር (PIN) የምመርጠው እንዴት ነው?

በአካባቢዎ የሚገኝ የማህበረሰብ DSHS አገልግሎት ጽ/ቤት (CSO) ጋር በመደወል ባለአራት አህዝ የግል መለያ ቁጥር (PIN) መምረጥ ይችላሉ፡፡ ለመገመት ቀላል የሆነ ለምሳሌ "1234" ወይም "0000" የግል መለያ ቁጥር (PIN) ወይም ማንኛውም ቀላል ኮድ አይጠቀሙ፡፡

### የግል መለያ ቁጥሬን ከረሳሁትስ?

የግል መለያ ቁጥርዎትን ከረሱት ወይም መቀየር ከፈለጉ፥ ወደ ደንበኛ አገልግሎት ማዕከል መደወል ይችላሉ።

### የተሳሳተ የግል መለያ ቁጥር PIN ካስገባሁስ?

የተሳሳተ የግል መለያ ቁጥር ካስገቡ፥ ትክክለኛውን ለማስገባት ሶስት ዕድል ይኖርዎታል። ትክክለኛው የግል መለያ ቁጥር (PIN) በአራተኛው ሙከራ ላይ ካልገባ ሂሳብዎትን ለመጠበቅ ካርዱ ይቆለፋል፡፡ በአካባቢው የሚገኝ የ DSHS ጽ/ቤት ሄደው የተቆለፈውን ካላስከፈቱ በስተቀር ከእኩለ-ሌሊት በፊት ካርድዎን በድጋሚ መጠቀም አይችሉም፡፡ በአንዳንድ አጋጣሚዎች ላይ ካርድዎት በኤ.ቲ.ኤም. ማሽን ውስጥ ሊቀር ይችላል። ካርድዎት ከኤ.ቲ.ኤም ማሽኑ ካልወጣ፥ ወደ ደንበኛ አገልግሎት ማዕከሉ ይደውሉ።

### ሌላ ሰው የግል መለያ ቁጥሬን ቢያውቀው ምን ማድረግ ይኖርብኛል?

ወድያውኑ ወደ ደንበኛ አገልግሎት ማዕከል በመደወል አዲስ የግል መለያ ቁጥር ይምረጡ ወይም ወደ **www.ebtedge.com**በመግባት ወይ ebtEDGE የሞባይል መተግበርያ በመጠቀም የግል መለያ ቁጥርዎን ይቀይሩት።

### ቀሪ ሒሳቤን እንዴት ነው ማወቅ የምችለው?

ቀላሉ መንገድ በየጊዜው የሚሰጥዎትን ደረሰኝ በማስቀመጥ ነው። ደረሰኞቹ ከሌሎት፥ ወደ **www.ebtedge.com** በመግባት ወይም e*bt*EDGE ሞባይል መተግበርያ በመጠቀም ወደ ደንበኛ አገልግሎት ማዕከል በመወደወል ቀሪ ሒሳብዎን ማወቅ ይችላሉ። ወደ ገበያ ከመሄድዎ በፊት ቀሪ ሒሳብዎን ማወቅ ይኖርብዎታል።

## የ Point of Sale (POS) ማሽኑ የማይሰራ ከሆነስ?

የምግብ ድጎማዎ ተጠቅመው የሚፈቀድልዎ የምግብ ዓይነት መግዛት ቢፈልጉም የPOS ማሽኑ የማይሰራ ከሆነ ወይም ሱቁ ውስጥ ማንም ሰው ከሌለ፥ ገንዘብ ተቀባዩ የምግብ ድጎማ ኩፖን የሚባል ፎርም ላይ ይሞላል። ገንዘብ ተቀባዩ የዋሽንግተን የQuest EBT ካርድዎት ላይ ቁጥር እና ያወጡትን የገንዘብ ልክ ይፅፋል። ለገንዘብ ተቀባዩ የግል መለያ ቁጥርዎን አይስጡት። ገንዘብ ተቀባዩ በምግብ ድጎማ ተቀማጭ ሒሳብዎ ላይ ያለውን ቀሪ ሒሳብ ምግብ ለመግዛት በቂ መሆኑ ለማረጋገጥ ይደውላል፤የጥሬ ገንዘብ ሒሳብ አይፈትሹም። የምግብ ድጎማ ተቀማጭ ሒሳብዎ ላይ በቂ ገንዘብ ካለ፥ ኩፖኑ ላይ እንዲፈርሙ ይጠየቃሉ፤ ቀጥሎም የኩፖኑ ቅጂ ይሰጥዎታል። በእጅዎ ካለው ከመጨረሻው የEBT መጠየቂያ ካርድ ጋር ተያይዞ የተሰጥዎትን ደረሰኝ ላይ ከተገለፀው ቀሪ ሒሳብ መቀነስ እንዲችሉ፥ ይህንን የኩፖን ቅጂ አይጣሉት። በደረሰኙ ላይ ከነበረው ሒሳብ ይህንን ኩፖን ላይ ያለውን ሲቀንሱት፥ አሁን ያለዎት ቀሪ ሒሳብ ማወቅ ይችላሉ። ሱቆች እርስዎ ለሚያወጡት ጥሬ ገንዘብ የሚሆን ኩፖን የላቸውም።

## ወደ ባንክ ሄጄ ገንዘብ ማውጣት ወይም ስለ EBT ተቀማጭ ሒሳቤ መጠየቅ እችላለሁ?

አይችሉም፥ ከኤ.ቲ.ኤም. ማሽን ወይም በመርሃ ግብሩ ተሳታፊ ወደ ሆነ ሱቅ በመሄድ ጥሬ ገንዘብ ብቻ ማውጣት ነው የሚችሉት። ስለ ጥሬ ገንዘብ ወይ የምግብ ጥቅሞች ሒሳብ ጥያቄ ካሎት ወደ ደንበኞች አገልግሎት ይደውሉ፡፡

## በዋሽንግተን የ Quest EBT ካርዴ ላይ ያለኝ ቀሪ ሒሳብ ከ10$ በታች ከሆነ፥ እንዴት ነው ማውጣት የምችለው?

በ POS ግዢ ሲፈጽሙ ወይም በመርሃ ግብሩ ተሳታፊ በሆኑት ሱቆች ላይ ጥሬ ገንዘቡን ማውጣት ይችላሉ።

## ከዋሽንግተን የ Quest EBT ካርዴ ከመጠቀሜ ጋር የተያያዘ ክፍያ ወይም ተጨማሪ ክፍያ መክፈል ይኖርብኝ ይሆን?

የዋሽንግተን የQuest EBTt ካርድዎትን ተጠቅመው ለሚገዙት ምግብ የሚከፍሉት የዝውውር ክፍያ የለም። የገንዘብ ድጎማዎትን ተጠቅመው ለሚገዙት ምግብ ወይም የPOS ማሽን ተጠቅመው ለሚያወጡት ገንዘብ የሚከፍሉት ነገር አይኖርም።

ተጨማሪ ክፍያ ሊኖር ይችላል፡፡ ተጨማሪ ክፍያ የሚከፍሉት፥ የኤ.ቲ.ኤም ማሽን ወይም የPOS ማሽን ባለቤት የሆነ ሰው ማሽኑን ተጠቅመው ገንዘብ ስላወጡ የሚያስከፍልዎት ይሆናል። ጥሬ ገንዘብ በማውጣትዎ ተጨማሪ ክፍያ መክፈል ቢኖርብዎትም፥ ክፍያው ከተቀማጭ ሒሳብዎ የሚቀነስ ይሆናል። ተጨማሪ ክፍያ መክፈል ካልፈለጉ ወደ ሌላ ኤ.ቲ.ኤም. ማሽን ወይም POS ማሽን ይሂዱና በነፃ ገንዘብዎትን ያውጡ።

## የ EBT የገንዘብ ድጎማየን ምን ጉዳዮች ላይ ማዋል አይኖርብኝም?

የEBT ካርድ ወይም ከEBT ካርድ የሚገኝ ገንዘብ በመጠጥ ቤቶች፥ በባሮች፥ በግሮሰሪ ቤቶች፥ የዋስ ቦንድ ድርጅቶች፥ በሴተኛ አዳሪ ቤቶች፥ በማንኛውም ከዕድሜ በታች ለሆኑ በተከለከሉት ቦታዎች ላይ፥ በቁማር ቤቶች፥ በንቅሳት ወይም ሰውነት መበሻ ቦታዎች፥ ወይም ትንባሆ ለመግዛት መዋል የሕግ ጥሰት ነው።

## ድጎማየን ካልተጠቀምኩበት ምን ይሆናል?

በወጣበት ወር ጥቅም ላይ ያልዋለ ድጎማ ወደ ቀጣዩ ወር ይተላለፋል። በ274 ቀኖች ውስጥ የተወሰነውን የድጎማ ገንዘቡን ካልተጠቀሙበት ድጎማው ይቋረጣል። በአንዳንዱ ሁኔታ ላይ፥ ድጎማው የማይመለስ ይሆናል።

## ወደ EBT ተቀማጭ ሒሳቤ ላይ ገንዘብ ገቢ ማድረግ እችላለሁ?

አይችሉም። ከተቀማጭ ሒሳቡ ወጪ ማድረግ ብቻ ነው የሚችሉት።

## ቀጥተኛ ገቢ ምንድን ነው?

EBT ከመጠቀም ይልቅ፥ የገንዘብ ድጎማዎትን በየወሩ በቀጥታ ወደ እርስዎ የባንክ አካውንት ገቢ እንዲደረግልዎት ሊመርጡ ይችላሉ። ቀጥተኛ ገቢን የምግብ ድጎማ ለማግኘት ሊጠቀሙበት አይችሉም። ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ ሰራተኞቹን ያነጋግሩ ወይም ወደ በነፃ ወደ 888-235-2954 ይደውሉ።

## አማራጭ ካርድ ያዥ ምንድን ነው?

አማራጭ ካርድ ያዥ ተብሎ የሚጠራ ሰው በመምረጥ በእርስዎ ምትክ ድጎማዎትን ሊቀበልልዎት ይችላል። አማራጭ ካርድ ያዡ ሰው ወደ አከባቢ ፅህፈት ቤት በመሄድ የራሱ የዋሽንግተን የQuest EBT ካርድ እና የግል መለያ ቁጥሩን መቀበል ይኖርበታል። አማራጭ ካርድ ያዥ የሚፈልጉ ከሆነ የሚያምኑት ሰው ይምረጡ። የጠፋ ወይም የተሰረቀ ድጎማ የማይመለስ መሆኑን ያስታውሱ። ወደ ደንበኛ አገልግሎት ማዕከሉ በመደወል አማራጭ ካርድ ያዡን ሊሰርዙት ይችላሉ።

## መቼ ነው ወደ ደንበኛ አገልግሎት ማዕከል መወደል የምችለው?

- ካርድዎ ከጠፋ፥ ከተሰረቀ ወይም ከተበላሸ።
- የግል መለያ ቁጥርዎን ከረሱት ወይ ከጠፋብዎት።
- የግል መለያ ቁጥርዎን ለመምረጥ ወይም ለመለወጥ።
- ቀሪ ሒሳብዎን ለማወቅ።
- በተቀማጭ ሒሳብዎ ላይ ለተደረጉት የመጨረሻዎቹን 10 ግብይቶች ለመስማት ይደውሉ።
- የሁለት ወር የተቀማጭ ሒሳብዎ የግብይት ታሪክ ለመጠየቅ።
- ስለ ዝውውር ጥያቄ ካሎት፡፡
- ከካርድዎ ጋር በተያያዘ ጥያቄ ካለዎት ወይም እገዛ ከፈለጉ።

## ወደ ሌላ ቦታ ለመቀየር ወይም አድራሻየን ለመለወጥ ካሰብኩስ?

ማንኛውንም ለውጥ፤ አድራሻዎትን መቀየር ጨምሮ ለማሳወቅ DSHSን በ 877-501-2233 በመደወል ወይ www.washingtonconnection.org በመጠቀም ኦንላይን ሪፖርት ያድርጉ፡፡

This pamphlet is available in your language at your local DSHS Office.

ይህ አስተኖ መጽሔት በቋንቋዎ በአካባቢዎ የዲኤስኤችኤስ ጽህፈት ቤት ይገኛል። (Amharic)

إن هذه النسخة موفرة لك بلغتك في مكتب الـ DSHS في الضاحية التي تسكن بها. (Arabic)

កូនសៀវភៅនេះមានផ្តល់ជូនជាភាសារបស់លោកអ្នកនៅនឹងការិយាល័យ DSHS ប្រចាំតំបន់របស់លោកអ្នក ។ (Cambodian)

本小冊備有您的語言版本，可向您當地的 DSHS 辦事處索取。(Chinese)

اين جزوه در زبان شما در اداره خدمات اجتماعي و درماني DSHS منطقه ايتان در دسترس مي باشد. (Farsi)

Dlaim ntawv nuav muaj txhais ua koj yaam lug hab nwg nyob rua ntawm lub DSHS kws ze koj ko. (Hmong)

이 팜플렛의 한국어 팜플렛은 귀하지역 관할 보건사회부(DSHS) 사무소에 비치돼 있습니다.(Korean)

ປື້ມຄູ່ມືຫົວນີ້ມີໄວ້ໃຫ້ໃນພາສາຂອງທ່ານຢູ່ທີ່ຫ້ອງການ DSHS ທ້ອງຖິ່ນຂອງທ່ານ. (Laotian)

ਇਹ ਪੈਂਫਲੇਟ ਤੁਹਾਨੂੰ ਮਿਲ ਸਕਦਾਂ ਹੈ ਆਪ ਦੀ ਭਾਸ਼ਾ ਵਿਚੱ ਆਪਣੇ ਸਥਾਨੀ DSHS ਦਫਤਰ ॥ (Punjabi)

Acest pamflet este disponibil în limba dumneavoastră la oficiul DSHS local. (Romanian)

Вы можете получить эту брошюру на своём языке в своём местном офисе DSHS.(Russian)

O lo'o maua le tusi lea i lau gagana i le ofisa o le Welfare (DSHS). (Samoan)

Ovaj pamflet je dostupan i na vašem jeziku u vašem mjesnom DSHS uredu. (Serbo-Croatian)

Waraaqahani waxaad ka helikartaa xafiiska Walfeerka, DSHS, ee kuu dhow, iyaga oo ku qorran afgaaga. (Somali)

Ang pamphlet na ito ay nakasulat rin sa Tagalog at makukuha sa tanggapan ng DSHS na pinakamalapit sa inyo. (Tagalog)

እዚ መጽሔት እዚ ብቛንቋኹም ኣብ ከባቢኹም ዝርከብ ቤት ጽሕፈት ዌልፈር ይርከብ (Tigrigna)

Ви можете одержати цю брошуру на своїй мові в своєму місцевому офісі DSHS.(Ukrainian)

Tập sơ liệu này hiện có bằng ngôn ngữ của quí vị tại văn phòng DSHS địa phương.(Vietnamese)

USDA እኩል ተደራሽነት ያለውና ስራ ፈጣሪ ነው።


Washington State Department of Social & Health Services

Transforming lives

©2021 FIS. All rights reserved.

DSHS 22-310 AM (Rev. 09/21) Amharic

# የዋሽንግተን Quest EBT መጠቀም




**የቅጣት ማስጠንቀቂያ፦**
**የ EBT ካርድ መሸጥ ወይም ለመሸጥ መሞከር ወይም የምግብ ድጎማን በሌላ ዋጋ ባለው ለምሳሌ ጥሬ ገንዘብ፣ እጽ፣ መሳሪያ ወይም ፈቃድ ካለው ሻጭ ከምግብ ሌላ ሌላ ነገር መለወጥ ወይም ለመለወጥ መሞከር ህገወጥ ነው፡፡ ሆንብሎ አላግባብ መጠቀም መባረር፣ የገንዘብ ቅጣት እና የህግ እርምጃ የወንጀል ክስን ጨምሮ ሊያስከትል ይችላል፡፡**

ስለ ተቀማጭ ሒሳብ መረጃ ከፈለጉ፥
ይህንን ድረገፅ ይጎብኙ፡-

**www.ebtedge.com**

**ወይ ebt EDGE ሞባይል መተግበርያውን ይጠቀሙ**

ወይም ወደዚህ ይደውሉ፡-

## የደንበኛ አገልግሎት ማዕከል

**888-328-9271**
**711 (TTY State Relay)**
**800-833-6385 (Telebraille)**